# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

***Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)***


መስከረም ፱ ቀን ፪ ሺህ ፲፩ ዓ. ም
September 19, 2018

## የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል

ከቅርብ ወራት በፊት በአገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ባልጠበቅነው ጊዜና መልኩ ተስፋ-ሰጭ የዴሞክራሲ ሂደት ተጀምሯል። ይህ የለውጥ ሂደት ሊበረታታና ሊደገፍ ይገባዋል።

ለሃያ ሰባት ዓመታት በጎሣ ፖለቲካ ታፍኖ የኖረን ኅብረተ-ሰብ፣ ወደተደላደለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ማሸጋገር ከፍተኛ ትዕግስትንና ከባድ ሥራን የሚጠይቅ መሆኑም ግልጽ ነው። በጥበብና በትዕግስት ካልተያዘ ደግሞ ይህ ሁኔታ ተቀልብሶ ወደነበረበት መቀመቅ ሊወርድ እንደሚችል በግልጽ መታወቅ አለበት።

ይህ እየታየ ያለው የለውጥ ሂደት ለአብዛኛው ሕዝባችን ልብ የሚሰርቅ የዴሞክራሲ ጭላንጭልንና ብሩህ ተስፋን ያበሰረልንን ያህል፣ በተቃራኒው ደግሞ ጥቅማ-ጥቅማቸው ለተነካባቸው እኩይ ኃይሎች እንደ እሬት እንደሚጎመዝዛቸው ማወቅ ይኖርብናል። ያለ የሌለ ኃይላቸውን ሁሉ በመጠቀም በሕዝባችን ላይ የስቃይና የመከራን ሥርዓት መልሰው ለማምጣት ያለዕረፍት ሌት ቀን በመሥራት ላይ መሆናቸውን በሚገባ ማጤን ይኖርብናል፣ በተግባር እየተካሄደ ያለና የምናየው ጉዳይ ነውና! ለዚህም ነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብትና ጥቅም ቆመናል የሚሉ ኃይሎች ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማስፈን እንዲቻል ሁኔታዎች እንዳይቀለበሱ ያለመታከት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ የሚኖርባቸው።

ስለሆነም በሀገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን የለውጥ ሂደት፣ የለውጡ ደጋፊ የሆነ የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ በተለያየ መልክ የተደራጁ ወገኖች፣ የትግሉን ውስብስብ ሂደት በሰከነ ሁኔታ በማጤን የጥፋት ኃይሎች ሁኔታውን እንዳያበላሹት ነቅተው መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

በመንግሥትም በኩልም በርካታ ስሜትን የሚቀሰቅሱና ቀልብን የሚስቡ ተስፋ-ሰጪ ሁኔታዎች ቢስተዋሉም፣ በሕገ-ወጥ ድርጊቶች የሰው ሕይወትና ንብረት ከመጥፋቱ በፊት የመከላከያ ዕቅድ መነደፍ ይገባው ነበር። ነገር ግን ይህ ባለመደረጉ፣ በየጊዜው ከፍተኛ


Phone : 0039035213311 00393297846515 Email:eprp@eprp-ihapa.com

ጥፋት እየደረሰ፣ ለምንታገልለት የዴሞክራሲና የመረጋጋት ሂደት እንቅፋት እየሆነ ነው። ትናንት በጅጅጋ የደረሰው የሰው ሕይወትና የንብረት ጥፋት፣ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ከቀየው ተሰዶ ስቃይና መከራ ላይ ሊወድቅ የቻለው መንግሥት ፈጥኖ መድረስ ባለመቻሉም ጭምር ነው። መንግሥት ፈጣን እርምጃ ወስዶ ቢሆን ኖሮ፣ ችግሩን ሙሉ በሙሉ ሊያቆመው ባይችልም፣ በሕዝብ ላይ የደረሰውን የጉዳት መጠን ሊቀንሰው ይችል ነበር ብለን እናምናለን።

ቀጥሎም፣ ሰንደቅ ዓላማን ምክንያት አድርገው ወጣቶች ግርግር ሲፈጥሩ፣ ችግር ፈጣሪዎችን ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት በቁጥጥር ሥር ማዋል በተገባ ነበር። ጊዜው ካለፈና መጥፎ የፖለቲካ አሻራ ከተጣለ በኋላ፣ ፖሊስ አጥፊዎቹ እነማን እንደነበሩና ለምንስ ዓለማ ያንን ግርግር እንደተጠቀሙበት ሲነግረን፣ በፀጥታ ኃይሎችም ውስጥ ለውጡን ያልተቀበሉ ሰርጎ-ገብ ክፍሎች ይኖሩ ይሆን? ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን።

ከሰሞኑ ደግሞ፣ በቡራዩና አካባቢው የተከሰተው ችግር በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። ብዙ ሰው ቆስሏል፣ በሕይወት የተረፈውም ሕዝብ ቢሆን መኖሪያ ቦታውን ለቆ ሜዳ ላይ ተበትኖ የስቃይና የመከራ ገፈት ቀማሽ እንዲሆን ተገዷል። ይህ ሕገ-ወጥ እርምጃ የተጀመረውን የለውጡን ሂደት ለማሰናከልና የቀን-ጅቦቹ አገሪቱን ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ለመውሰድ የሚያደርጉትን ጥረት በግልጽ ያመለክታል። የፖሊስ ኮሚሽነሩ ጋዜጣዊ መግለጫም እያረጋገጠልን ይህንኑ ሃቅ ነው።

መንግሥት ይህንን እኩይ ተግባር በሚጠነሰሱ ኃይሎች ላይ በአስቸኳይ ሕጋዊ እርምጃ ካልወሰደ በስተቀር፣ በአሁኑ ጊዜ የሚታየውን ሕዝባችን የሚሰማውን የመረጋጋት ስሜትና የሰላም አየር የመተንፈስ ተስፋ ሳይውል ሳይድር ደብዛው ሊጠፋ እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ ልናሳስብ የምንሻው፣ የተጀመረው የለንውጥ ሂደትና የሕዝቡን የመረጋጋት ስሜት ዘለቄታ እንዲኖረው በማድረግ አኳያ መንግሥት ብቻውን፣ ምንም ያህል ተግቶ ቢሰራም፣ ዋስትና ሊሰጥ እንደማይችል ነው። ደግመን ደጋግመን እንዳሳሰብነው የሃይማኖት አባቶች፣ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማኅበራት መሪዎችና ሌሎችም አገር ወዳድ ዜጎች የሕዝቡን ሰላም ለማስጠበቅ ከሕግ አስከባሪ ኃይሎች ጋር

በመተባበር በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል። ዴሞክራሲና ሰላም ወደ ሕዝብ የሚዘልቁት በዚህና በዚህ መንገድ ብቻ ነውና።

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በጥፋት ኃይሎች ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ወገኖቻችንን ነፍስ ይማር ይላል። ለቤተሰቦቻቸውንም መጽናናትን ይመኛል።

ዴሞክራሲ በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ እንጂ በግርግር አይገነባም!